
ADV3

አዲስ የልማት ራዕይ
አዲስ ቪዥን ለርኒንግ ማቴሪያልስ ማኑፋክቸሪንግ

Addis Development Vision

# ጂኦግራፊና ታሪክ



አዲስ አበባ
ጥር 2003 ዓ.ም መጀመሪያ ታተመ
መስከረም 2009 ዓ.ም እንደገና ታተመ



ማወቅ የሚገባዎት
ትልቅ ቁም ነገር!

Addis Development Vision

አዲስ ዴቨሎፕመንት ቪዥን/ አዲስ ቪዥን ለርንኒግ ማቴሪያልስ ማኑፋክቸሪንግ በሙያ ስልጠና ማዕከሉ ዉስጥ የህፃናት ትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በማምረት ለኢንተርናሽናል፣ ለመንግስታዊና ለግል መዋዕለ ሕፃናት ድርጅት የትምህርት መርጃ መሳሪያ ገዢዎችን ጥያቄ በማስተናገድ ላይ ይገኛል::



የወቅቱን የሕፃናትና ልጆች እዉቀት ለማስጨበጥ ያስችላሉ የተባሉትን ማስተማሪያ አዲስ ዘይቤ ያካተተ መሆኑ አስተማማኝ ያደርገዋል::



ምርታችን ጥራት አስተማማኝና ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን የጠበቀ ሲሆን በትምርትና በሞያ ስልጠና የተሰማሩ ባለሙያዎች የረጅም ጊዜ ልምድ ዉጤት ነዉ::

መርጃ መሣሪያዎቹ የዘመናዊ ትምህርት አሰጣጥ ስልትን ያገናዘቡ በመሆናቸዉ ለመዋዕለ ሕፃናትና ዕድሜያቸዉ እስከ 10 ዓመት ለሆናቸዉ ታዳጊ ልጆች ማስተማሪያነት ማገልገል ያስችላል::



በተጨማሪም ድርጅታችን በትምህርት መርጃ መሳሪያዎች አጠቃቀምና ለመዋዕለ ሕፃናት መምህርነት ስልጠናዎችን ይሰጣል::

ከ1990 ዓ/ም ጀምሮ በርካታ ት/ቤቶች ተጠቅመዉ በዉጤቱ ሲረኩበት በምርታችን እንኮራበታለን:: እናንተም ተጠቀሙበት ዉጤታማነታችሁን ያሳድጋል::

ISBN 978-99944-861-3-7

Printing by:- Star Printing Press

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎቹ ከዚህ እንደሚከተሉት አምስት ዋና ክፍሎች ይኖሩታል፡፡

I. የተግባራዊ እንቅስቃሴ መሳሪያዎች
II. የስሜት እንቅስቃሴ መርጃ መሳሪያዎች
III. የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች
IV. የሒሳብ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች
V. የሳይንስ ትምህርት መርጃ መሳርያዎች

## (V) የጂኦግራፊና ታሪክ ቅርሶች

የአለምን ሁኔታ ለማወቅና ለመመርመር የባሕል አካባቢ ወይም ማዕከል ለሕፃናት ክፍት መሆን ይኖርበታል፡፡ ይህ ደግሞ ሕፃኑ የአለምን ጂኦግራፊ ታሪክ ወዘተ እንዲያውቅና እንዲረዳ ብሎም እንዲመራመር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪ የአለምን እድገት ለውጥ በመገንዘብ ለመኖር ምቹ ሁኔታ እንዲፈጥሩ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

ትላልቅ ሰዎች መልካም አካባቢን በመፍጠር ሕፃኑ ተስማምቶትና ተመቻችቶ እንዲኖር ወሳኝ ተግባራትን ማከናወን ይኖርባቸዋል፡፡ በባህላዊ ቁሶች ሕፃኑ ስሜታዊ የሆኑ ዕድሜዎቹን በእርካታ ያሳልፋል፡፡ ለምሳሌ የመሬትና የውሃ ገፅ፣ በአሸዋ የተሰሩ ቅርፆች፣ ተገጣጣሚ ካርታዎች ወዘተ የመሳሰሉት ስሜታዊ እድገቶችን ከፍ ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል፡፡ ባሕላዊ አለማችንን በማወቅ በባሕላዊ ቁሶች ሕፃኑ ከአእምሮው ጋር ማዋሃድና መከፋፈል ይችላል፡፡ ሕፃኑን ይህ ሁኔታ አካባቢውንና አለምን በማድነቅ፣ ራስን በማመሳሰል፣ ከተቻለም በመለወጥ መኖር እንዲችል ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው ፡፡

**ባሕላዊ ቁስ በሚስብ መልክና በጥሩ ሁኔታ ማቅረብ ይኖርበታል**

1. **አቀራረብ**
   - ትክክለኝነትንና ፍፁምነትን በማሳየት ሕፃኑ ነፃ እንዲሆንና በቁሱ ደስተኛ ከሆነ እንቅስቃሴውን ደጋግሞ ይሠራል፡፡ ደጋግሞ መስራት (ልምምድ) ወደ ብቁነት ስለሚያመጣ፣ ሕፃኑ ደጋግሞ ከሠራ ብቁ ይሆናል እንቅስቃሴውንም ይለምደዋል፡፡
2. **ስሕተትን መቆጣጠር**
   - ሕፃኑ ፍፁም ነፃ በመሆንና በማበረታታት ደጋግሞ እንዲሠራ መርዳት
   - ለሥራው ትጉህ እንዲሆንና ለስሕተቱ መፍትሄ እንዲፈልግ መርዳት
3. **ቋንቋ**
   - ባሕላዊው ቁስ ሕፃኑን በቃላት ብቁ እንዲሆኑ ይረዳል፡፡
   - ረዳት መምህራኑ ትክክለኛ ቃላትን እንዲጠቀሙ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ደግሞ በሰፊው የማንበብና የመፃፍ ብቃቱን ያዳብራል፡፡
4. **የቋንቋ ተግባር**
   - ከባሕላዊ ቁስ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ለምሳሌ የእቃዎቹን፣ የሰዎችን፣ የአገርን ወዘተ ትክክለኛ ስም መንገር

- አለም በአምስት ዋና ክፍሎች ይከፋፈላል፡፡ እነርሱም አለም፣ የአለም እፅዋት፣ የአለም እንስሳት፣ የአለም ስዕል፣ የአለም ሙዚቃ ናቸው፡፡

**አለም፤-**

- በክፍላችን፣ ሕፃኑ ለመጀመሪያ ጊዜ ሁሉንም በጥቅል ከተመለከተ በኋላ በመቀጠል እየቀናነሰ በዝርዝር ይመለከታል፡፡ ለምሳሌ በመጀመሪያ ስለ ውሀ እና መሬት እናስተዋውቃለን በመቀጠል ስለመሬትና ውሃ አፈጣጠር እናስረዳቸዋለን፡፡ ከብዙ ልምምድ በኋላ በአሸዋማ ወረቀት የተሠራውን ሉል እናሳያቸዋለን፡፡ በዚህ ምስል ሕፃኑ ስለአለም እውቀት ይኖረዋል፡፡ አለም ክብ መሆኗን አለም በመሬትና በጣም ሰፊ በሆነ ውሃ የተከፋፈለች እንደሆነች ያረጋግጣል፡፡ ሉል በማሳየት አለም በተለያዩ የአለም ክፍሎች (አሕጉሮች) እንደተከፋፈለች ሕፃኑ እንዲያውቅና እንዲረዳ ያግዛል፡፡ ከብዙ ልምምድ በኋላ ሕፃኑ የአሕጉሮችን ተገጣጣሚ ካርታ ያገኛል፡፡ በዚህ የመርጃ መሳሪያ ሕፃኑ ስለአለም አሕጉሮች

**መልመጃ 1:-**

- የሕፃኑ ተግባር ከላይ እንደታየው ይሆናል::

**ቋንቋ:-**

- የመሬትና የውሃ ስሞችን ለምሳሌ ሐይቅ፣ የባህር ወሽመጥ፣ ደሴት ወዘተ

**እድሜ:-**

- 4 አመት

## 3. <u>የመሬትና የውሃ ስካባት ሉል</u>

**መርጃ መሳሪያ:-**

- አንድ ሉል፣ የሚቀመጥ ወይም ዘንበል ብሎ የሚቆም
- ሰማያዊው ውሃ እና አፈራማው ወረቀት ደግሞ መሬትን ይወክላሉ



**አላማ:-**

- የአለም አካል ውሃ እና መሬትን መያዝን በማወቅ ስሜታዊ አድናቆትን በሕፃኑ ለማሳደር::
- የአለም ቅርፅ ክብ መሆኑን እንዲገነዘቡ ለማድረግ

**አቀራረብ**

- በጣታችሁ በመንካት ስሜት እንዲኖረው አድርጉ
- እረዳት መምህርቷ «ይህ የምንመለከተው አላማችንን ነው» ካለች በኋላ ቀስ በማለት ሉሉን በማዞር
- በጣታችሁ የመሬት አካልን ጠቁሙ
- የአለምን መሬት እንዲመለከቱ በመንካት እንዲሰማቸው አድርጉ:
- ቀስ ብላችሁ ሉሉን በማዞር የውሃውን ክፍል ጠቁሙና «ይህ ውሃ ነው»በሉት
- ህፃኑን የውሃውን ክፍል እንዲጠቁም ጠይቁት
- «አለማችን የተሠራው በውሃና በመሬት ነው» በማለት ጨርሱ::
- ሕፃኑ ከሉሉ ጋር እንዲሠራ ጋብዙት::

**መልመጃ 1**

- የሕፃኑ ሥራ እንደ አቀራረቡ መሆን ይኖርበታል

**ቋንቋ**

- መሬትና ውሃ

**ስሕተትን መቆጣጠር**

- የሉሉ አካል

**እድሜ:-**

- 4½ አመት ከበቂ ልምምድ በኋላ

በማዛመድ እንደሚሳይ ማሳየት

<u>መልመጃ 1</u>

- እንቅስቃሴው ከላይ እንዳየው አቀራረብ ነው

<u>መልመጃ 2</u>

- ሕፃኑ ስም ሳይኖረው ካርታውን ይሠራል
- ለማዝለብ ከፍተኛ ስሜት አለው ስለዚህ አበረታቱት

<u>ስሕተትን መቆጣጠር</u>

- የመጀመሪያው ስም ያለው ካርታ

እድሜ

- 4½ - 5 አመት

## 11. <u>የሰሕጉሪ ሰንደቅ ሰላማ</u>



<u>መርጃ መሳሪያ:-</u>

- የእያንዳንዱ አገር ሰንደቅ አላማ
- የሕፃኑ አገር (የኢትዮጵያ) የፐዝል ካርታ

አላማ

- የአፍሪካን ወይም ሕፃኑ የመጣበትን አሕጉር ሰንደቅ አላማ ለማስተማር
- ሰንደቅ አላማን በማድነቅ እንዲያከብር ለመርዳት

አቀራረብ 1

- በመጀመሪያ የሚሰራው በሕፃናቱ ሕብረት ነው
- ሰንደቅ አላማን እንዴት እንደሚይዝ አሳዩት
- ትርጉሙን አስረዱት፣
- ለምን እንደሚጠቅምም ንገሩት (የአንድ አገር አርማ መሆኑን)
- የአገርን ታሪክ መግለፁን መንገር

አቀራረብ 2

- ሕፃኑ ከእናንተ ጋር እንዲሰራ ጋብዙት
- የአገሩን ፐዝል ካርታ እና የአገሩን ሰንደቅ አላማ አግኙ
- ስለ ሰንደቅ አላማ ከአገሩ ጋር በማዛመድ በሦስት ክፍለ ጊዜ አስተምሩአቸው

<u>ለምሳሌ፡</u> - የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ

<u>መልመጃ 1</u>

- ሕፃኑ እንደ አቀራረቡ ይሠራል

እድሜ፡ - 4½ አመት

## 12. የዓለም ሕዝብ



*መርጃ መሳሪያ*

- በክፍለ አሕጉር ያለ ስፍራ፣ አለባበስ የሚያሳይ አካባቢ፣ ምግብ፣ የግቢ አበባ፣ የተወሰነ አካባቢ ባህልና የአየር ፀባይ

አላማ

- ሕፃኑ አለም አቀፋዊ መረዳት እንዲኖረው ወይም በዚያ አካባቢ የሚኖሩትን ሕዝቦች እንዲያውቅ ለማበረታታት

አቀራረብ

- ስዕሉን ጠረጴዛ ላይ ወይም ምንጣፉ ላይ ማስቀመጥ
- ሕፃኑ እንዲመለከተው መርዳት
- በስዕሉ የሚያዩትን ነገሮች እንዲናገሩ መጠየቅ
- መወያየት፡- ውይይቱ ወደ አየር ፀባይና ሁኔታ፣ የሚበቅለውን ፍራፍሬ፣ የሚለበሰውን የልብስ አይነት ወዘተ ወደ ማወቅ ደረጃ ያመራል።
- ጠቅላላ ውይይቱ ሕፃናቱ ስለተለያዩ አገሮች እንዲያስቡ እንዲሁም የአለም አየር ሁኔታን እንዲያውቁ ያደርጋል
- የበለጠ እንዲመራመሩ መንገድ ይጠረጋል

እድሜ፡ -

- 5 አመት

## 13. የጊዜ መስመር

*መርጃ መሳሪያ*

- የግራፍ ወረቀቶች (እስኩዌር ወረቀቶች)፣ ባለከለር እርሳስ፣ ኮላ፣ ፎቶግራፍ፣ መቀስ

አላማ

- ስለራሱ ታሪክ እንዲገነዘብና ስለ ታሪክ ጥሩ ግንዛቤ እንዲኖረው ለማድረግ

አቀራረብ

- የሚያስፈልጉትን ቁሶች ማዘጋጀት
- ለሕፃኑ ማስተዋወቅ
- ግራፉን አሳዩት
- እንዴት እንደሚሠራና እንደሚቀጣጠል አሳዩት
- ስሙንና እድሜውን የት እንደሚፅፍ ማሳየት
- ሕፃኑ ፎቶግራፍ ከመጣ ወላጆቹ ስለ ፎቶግራፍ አንዳንድ መረጃዎች እንዲፅፍ መጠየቅ
- ሕፃናቱ የሚወዱትና የሚመርጡትን ፎቶግራፍ እንዲያመጡ ማድረግ
- በእያንዳንዱ ፎቶግራፍ ሥር የሚፈልጉትን ነገር እንዲፅፉ መገፋፋት
- በመቀጠል ሕፃኑ ስለ ቤተሰቡ ወይም ስለ ጓደኞቹ መግለጽ ይችላል

- በቤት ውስጥ የተለያዩ ምግቦችን እናስቀምጣለን
  ለምሳሌ ሳርና ቅጠሎች ወዘተ
- ውሃ መጠጫ ገንዳ እናዘጋጃለን
- በጉ ሳር ይበላል

## የተግባር እንቅስቃሴ

- ሕፃናቱ የበጉን መኖሪያ እንዲያፀዱ ማዘጋጀት
- መጠጫውን እንዴት እንደሚያፀዱ ማሳየት
- ምግብን በምን መልክ እንደሚሰጡ ማሳየት
- በሩን እንዴት እንደሚከፍቱና እንደሚዘጉም ማሳየት

## ስሜታዊ እንቅስቃሴ

- ለሕፃናቱ በጉን እንዴት እንደሚነኩና እንደሚዳስሱ ማሳየት ምክንያቱም በጎች አደገኞች አይደሉም

## ወፎች

- በላባ የተሸፈኑ፣ ሁለት ክንፍ፣ ሁለት እግሮች ያሏቸውና አብዛኛዎቹ መብረር የሚችሉ ናቸው
- ወፎች የመኖሪያ ጎጆ በመስራት የሚኖሩ ናቸው
- ቤታቸውን ዛፍ ላይ በመስራት ይኖራሉ
- እናት ወፍ ልጇን የተለያዩ ምግቦችን በማምጣት ታበላለች
- ሁሉም ወፎች ያለ ችግር የሚኖሩበትን ስፍራ ይመርጣሉ
- በመኖሪያቸው ቦታ እንቁላል ይጥላሉ
- በእነርሱ በጣም እንደሰታለን
- ጥሩ መኖሪያቸው ዛፍ ላይ ነው
- ጥሩ የመመልከት ችሎታ አላቸው
- እንደ አየሩ ሁኔታ የመኖሪያ አካባቢያቸውን ይቀያይራሉ
- መሬት ላይ ይኖራሉ ውሃ ውስጥም መኖር ይችላሉ
- በመብረር ብዙ እርቀት ይጓዛሉ
- ወፎች ደመ ሞቃት እንስሳት ናቸው
- የሚመገቡት ጥራጥሬ፣ ፍራፍሬ ወ.ዘ.ተ. ነው

### <u>የወፎች ስኗኗር</u>

- ወፎች የሚኖሩት በሕብረት ነው
- እርስ በርሳቸው የሚገናኙት በመዘመር ነው፡፡
- የራሳቸው መግባቢያ ቋንቋ አላቸው

## <u>እንዴት እንመግባቸዋለን?</u>

- ለመመገብ ጠረጴዛ እናዘጋጃለን
- በአትክልት ስፍራችን ዝርግ ሳህን ወይም ትሪ እናዘጋጃለን
- ከድመትና ከመሳሰሉ ከሚያጠቋቸው እውሬዎች ወፎችን መጠበቅ ይኖርብናል
- ምግባቸውን ግድግዳ ላይ መስቀልም እንችላለን

- ከዚያ መመገብ ይችላሉ::

## የተግባር እንቅስቃሴ

- ከተመገቡ በኋላ ጠረጴዛውን እንዴት እንደሚያፀዱ ማሳየት
- ሕፃኑ ውሃ እንዴት እንደሚሰጣቸው ማሳየትና ውሃውን በማስቀመጫ ማስቀመጥ

**አሳ**

- የመጀመሪያዎቹ ከአጥንት አልባዎችም ሆነ የጀርባ አጥንት ካላቸው የሚመደቡ ናቸው::
- የዛሬ 5 ሚሊዮን አመት አካባቢ የነበሩ ናቸው
- በአሁኑ ወቅት 27 ሺህ የተለያዩ ዝርያዎች በውሃ ውስጥ ይኖራሉ
- ከሌሎቹ ሁሉ በትልቅነትና በአይነት ይበልጣሉ

<u>የአሳ ነባሪ</u>

- መኖሪያው ውሃ ውስጥ ብቻ ነው
- የሚበላው፣ የሚጠጣውና የሚተነፍሰው በስንጥቡ ብቻ ነው
- መዋኛ ጭራ አለው
- በጣም ብዙ የተለያዩ አሳዎች አሉ::
- አሳዎች ደመቀዝቃዛ እንስሳት ሲሆኑ የሚተነፍሱትም በስንጥባቸው ነው
- ሰዎች አሳዎችን ለምግብነት ይጠቀሙባቸዋል
- የአሳ አይነቶች ለምሳሌ ወርቃማ አሳ፣ አሳነባሪ፣ ጀሊ ፊሽ ወ.ዘ.ተ. ናቸው::

<u>ወርቃማ አሳ</u>

<u>መርጃ መሳሪያ</u>

ወርቃማውን አሳ ለማኖር የሚያስፈልጉ ነገሮች

- ትልቅ በመስታወት የተሰራ ጎድጓዳ ገንዳ
- ትናንሽ ድንጋዮች
- አሸዋና የተዘጋጁ ምግቦች ናቸው

**አቀራረብ**

- ለሕፃናቱ ስዕሉን ለማሳየት ቦታ መርጦ ስእሉን በመሳል ማሳየት
- ሕፃናትን የአሳ መኖሪያን በሕብረት እንዲያዘጋጁ ማበረታታት
- እንዴት እንደሚመግቡትና እንቅስቃሴውን እንደሚመለከቱ አለማምዷቸው
- በየቀኑ ምን ያህል ውሃ እንደሚያስፈልገውም ንገሩት
- ውሃው እንደሚቀየር አሳዩዋቸውና በሚቀጥለው ቀን ልጆቹ ራሳቸው ይቀይሩት
- የተለያዩ ስዕሎችን በማሳየት ሕፃናቱን አስተምሩአቸው
- የተለያዩ የአሳ ክፍሎችን ስንጥብ፣ መዋኛ አካል፣ ጭራ ወዘተ
- ሕፃናቱን ስሜታዊ አመለካከት ለማዳበር በውሃና በመሬት የሚኖሩ እንስሳት ተራማጅ እንስሳት እንደ እንቁራሪት፣ ጉርጥ ወዘተ ናቸው
- በውሃና በመሬት ላይ መኖር ይችላል
- እንቁላል ከጣሉ በኋላ ወይም ከተፈለፈለ በኋላ በራሳቸው ያድጋሉ
- ቋሚ የሰውነት ሙቀት የላቸውም

- በእንስሳት ላይ ፍላጐት እንዲኖራቸው ለመርዳት

አቀራረብ፡-

- የተለያዩ ወፎችና እንስሳትን መምረጥ
- አረዳት መምህርቷ በእጇ ይዛ ማወቅ አለማወቃቸውን መጠየቅ ከዚያ ምንጣፍ ላይ ማስቀመጥ
- መኖሪያ ቦታቸው መታወቅ አለበት
- ዘወትር የሚበሉትን ምግብ ቀለም ይለያሉ
- ካላወቁ በሦስት ማስተማሪያ ዘዴ ማሳወቅ ያስፈልጋል

መልመጃ አንድ ፡-

- ሕፃኑ እንደ አቀራረቡ ይሠራል

ቋንቋ፡-

- የእንስሳትን ስም

እድሜ፡-

- 4 - 4½ አመት
- እንስሳትን በስማቸው መከፋፈል

መርጃ መሳሪያ፡-

- የካርዶች ስብስብ 5 አይነት እንስሰትን የያዘ
  አጥቢ፣ አሳ፣ ወፎች፣ ተሳቢና ተራማጅ እንስሳት
- ስብሰብ አንድ የሚይዘው ስዕሎችን በካርድ በመከፋፈል
- ስብስብ ሁለት የሚይዘው ስብስብ አንድ ላይ ያሉትን ስዕሎችና
  መቆጣጠሪያ ካርድ የሚጠቅመውም ስእሉንና ስሙን ለማገናዘብ

አላማ፡-

- የሕፃኑን የቃላት ችሎታና የማንበብ ብቃቱን ለማሳደግ

አቀራረብ፡-

- ስዕሉንና ስሙን በማንበብ ማዛመድ
- በተከፋፈሉ ካርዶች ሕፃኑ ይሠራል

ስሕተት መቆጣጠር፡-

- ስም ያላቸው የካርዶች ስብስብ

እድሜ፡-

- 5 - 5½ አመት

  **ማብራሪያ 1**

መርጃ መሳሪያ፡-

- መያዣያው /ማቀፊያው/ 5 ስዕሎችን የአምስት እንስሳትን በ5 ካርዶች ከነመግለጫቸው የያዘ ነው፡፡
- ቁሱን ማዘጋጀት፤ ሲዘጋጅ ከውሃና ከመሬት አመሰራረት መግለጫ ጋር ይመሳሰላል
- መጽሐፍ ያለ መግለጫ

አላማ፡-

- ሕፃኑ አካባቢውን ለመመደብ እንዲችል መርዳት
- ለእንስሳቱ ያለውን ፍላጐት እንዲያሳድግ ለመርዳት

አቀራረብ፡-

- ሕፃኑ የእንስሳቱን ስዕል ካየ በኋላ ምንጣፍ ላይ እንዲያስቀምጥ መርዳት
- ካርዱ ላይ ያለውን መግለጫ ከስዕሉ ጋር ማዛመድ

<u>ስሕተትን መቆጣጠር</u>፡-

- የመጽሐፍን መግለጫ መጠቀም

<u>እድሜ</u>፡-

- 6 - 6½ አመት

<u>ማብራሪያ 2</u>

<u>መርጃ መሳሪያ</u> ፡-

- ማቀፊያው አምስት የተለያዩ እንስሳት ምስል የያዘ አምስት ስዕሎች
- አምስት ርዕሶች ማብራሪያ የሌላቸው
- ቁርጥራጭ ወረቀቶች ርዕሶቹ በቀይና ስማቸው በጥቁር የተፃፈባቸው
- የትርጉም /የማብራሪያ/ መጽሐፍ

<u>አላማ</u> ፡-

- የሕፃኑን አንድን ነገር አንብቦ የመረዳት ብቃቱን ለማሳደግ

አቀራረብ፡-

- ስዕሎቹን ምንጣፉ ላይ ለመግለጫ ካርዶቹ ቦታ በመተው ማጋደም
- የመግባባት ካርዶቹን በማንሳት በቦታው በጥቁርና በቀይ የተፃፈውን ትናንሽ ወረቀቶችን ማስቀመጥ
- መግለጫ ካርዱን ለሕፃኑ በመስጠት እንዲያነብ ማድረግ
- ከየትኛው ስዕል ጋር እንደሚዛመድ እንዲለይ መርዳት
- ከዚያ በቦታው መግለጫውን ከስዕሉ ጋር ማዛመድ
- ደጋግሞ በማንበብ ትክክለኛውን ርእስ ማግኘትና ማዛመድ

<u>ስሕተተን መቆጣጠር</u>፡-

- የመጽሐፉን መግለጫ /ትርጉም/

እድሜ ፡-

- 6 - 6½ አመት

<u>ማብራሪያ 3</u>

<u>መርጃ መሳሪያ</u> ፡-

- ማቀፊያው የማብራሪያ ካርዱን የያዘ
- ትናንሽ ወረቀቶች ላይ አርዕስት በቀይና በጥቁር ቀለም መፃፍ
- የትርጉም /መግለጫ/ መጽሐፍ

<u>አላማ</u> ፡-

- ሕፃኑ የማንበብ ልምምዱን ያዳብራል
- የህፃኑን ቅደም ተከተል የማወቅ ብቃት ማሳደግ

<u>አቀራረብ</u> ፡-

- ሕፃናቱ አምስቱን ስዕሎች እንዲያስቀምጡ መጋበዝ
- ቀይና ጥቁር ርዕስ ያላቸውን ማምጣት
- በመጀመሪያ ርዕሱን ምረጡ
- ከዚያ ትክክለኛውን ርዕስ ከወረቀቱ ላይ በመውሰድ መግለጫውን ማዳበር

- እረዳት መምህርቷ ታቋርጥና ሕፃኑ በተመሳሳይ መልክ ይቀጥላል።

<u>ስሕተትን ለመቆጣጠር</u>፡-

- የመጽሐፍን ትርጉም

እድሜ፡-

- 6 - 6½ ዓመት

**የእንስሳትን የሰውነት ክፍሎች ስዕል**

<u>መርጃ መሳሪያ</u>፡-

- ማቀፊያው የእንስሳትን ዋና ዋና ክፍሎችን ምስል ይይዛል
- በእያንዳንዱ ማቀፊያ ከ5 እስከ 6 ስዕሎች መማለጫ እንደሁም እንስሳት የሰውነት ክፍሎች እያንዳንዱ በተለያዩ ቀለሞች የተቀባ ይሆናል

አላማ ፡-

- ሕፃኑ ስለ እንስሳት ያለውን እውቀት ለማስፋት
- ስለ እንስሳት ዓላማ ያለውን ፍላጐት ለማዳበር
- ሕፃኑ እንስሳቱን የበለጠ መከፋፈል እንዲችልና እንዲመራመር ለመርዳት

<u>አቀራረብ</u>፡-

- በመጀመሪያ ሙሉ በሙሉ የተቀባውን እንሰሳ ማስተዋወቅ
- ስማቸው ምንጣፉ ላይ ወይም ጠረጴዛው ላይ መቀመጡን ማረጋገጥ
- ከዚያ የእንስሳውን ክፍሎች ወይም የአሳን ክፍሎች ማስተዋወቅ
- በመቀጠል ተራ በተራ የሁሉንም እንስሳት ክፍሎች እስኪያውቁ ድረስ ማስተማር

መልመጃ 1

- ሕፃኑ ከካርዱ ጋር ይቀጥላል

<u>ቋንቋ</u>፡-

- የእንስሳትን የሰውነት ክፍሎች በሶስት ክፍለ ጊዜያት አስተምሯቸው

<u>እድሜ</u>፡-

- 4 ዓመትና በላይ

<u>እፅዋት</u>

<u>መርጃ መሳሪያ</u>፡-

- እውነተኛ እፅዋትና የእፅዋትን ክፍሎች የሚያመለክት ካርድ

<u>ቀጥተኛ ዓላማ</u>፡-

- ሕፃኑን ትክክለኛ የእንስሳት ክፍሎችን ስም እንዲያውቁ ለማስተማር

ኢ - ቀጥተኛ ዓላማ፡-

- ስለ እፅዋት ትምህርት ለማዘጋጀት

<u>አቀራረብ</u>፡-

- ዝግጁ የሆኑትን ሕፃናት መጋበዝ

* አንዱን አትክልት ወደ ጠረጴዛ /ምንጣፍ/ በማምጣት ከሕፃናቱ ጋር ስለ እያንዳንዱ ክፍል ማለት ስለ ቅጠል፣ ሳር፣ ቅርንጫፍ፣ ግንድ ወዘተ መነጋገር
* እፅዋቱን ማስቀመጫ ጠረጴዛ ላይ ማስቀመጥ
* በሚቀጥለው ቀን ካርዱን በማውጣት ለሕፃናቱ ከትክክለኛው እፅዋት ጋር በማዛመድ ማስተዋወቅ
* ስለ እፅዋት ትክክለኛውን ስም እስኪያውቁ ድረስ በሦስት ማስተማርያ ዘዴ አስተምሯቸው

**መልመጃ አንድ፡-**

* ሕፃኑ ሥራውን እንዲያቀርብ ማበረታታት

**ስሕተትን መቆጣጠር፡-**

* ሲያቀርብና ሲመለከት

**ቋንቋ፡-**


* የእፅዋት ክፍሎች ስም

## 15. የዓለም እፅዋት

**ቅድመ ንባብ**

**መርጃ መሳሪያ፡-**

* የአበባዎች፣ የዛፎች፣ የቅጠሎች ወዘተ ስዕሎችን የያዙ ካርዶች ስብስብ
* የተለያዩ የእፅዋት ክፍሎችን ያየዙ፣ የእፅዋትን ስም በጥቅል የያዙ ካርዶች




**አላማ ፡-**

* የሕፃኑን የቋንቋ ችሎታ ለማዳበር
* ስለ አለም እፅዋትና ዛፎች የሚኖራቸውን እውቀት ለማዳበር

**አቀራረብ፡-**

* ከአለም እንስሳት አቀራረብ ጋር ተመሳሳይ ነው
* የተለያዩ አበባዎችን ስም መንገር

**ምሳሌ፡-**

* ፅጌረዳ አበባ፣ ሊሊ አበባ ወዘተ. . .

**መልመጃ አንድ ፡-**

* ሕፃኑ እንደ አቀራረቡ ይሰራል

**ቋንቋ፡-**

* የአበባ ስም

**እድሜ፡-**

* ከ 4½ በላይ

የተከፋፈሉ ካርዶች

መርጃ መሳሪያ:-

- ስለ አበባዎቹ የሚገልፁ ካርዶች እንዲሁም ሰፋ ያሉ መግለጫዎች ይኖራቸዋል

ምሳሌ:-


- እፅዋት፣ ግንድ፣ ቅጠል፣ ቅርንጫፍ

አላማ:-

- ሕፃኑ ስለ አካባቢው የሚኖረው እውቀት ይዳብራል
- ለወደፊቱ ምርምር መሠረት ለማስያዝ

አቀራረብ :-

- አቀራረቡ ከእንስሳቱ አቀራረብ ጋር የተመሳሰለ ነው
- የእፅዋት ክፍሎች ሲቀርብ የአካባቢውን አትክልት ማዘጋጀት
- ከአትክልት ቦታ አንድ አበባ ምረጡ
- ስለ አበባው ግለፁ
- በመቀጠል ካርዱን ከፋፍሉት




መልመጃ አንድ :-


- እንደ አቀራረቡ ሕፃኑ በካርዱ ሥራ ይሠራል

143 የእፅዋት ብቅለት ሙከራ (Experiment)

መርጃ መሳሪያ:-

- ሁለት ጣሳ፣ ያልተሰባበረ ጥራጥሬ፣ ውሃ

አቀራረብ:-



- በሙከራ ወቅት የሚሳተፉትን ሕፃናት ጋብዙ
- በሁለቱም ጣሳዎች ውስጥ ጥራጥሬውን ሁለት ቦታ በመክፈል እንዲጨምሩ ንገሩአቸው
- ጥራጥሬውን ከጨመሩ በኋላ በአንዱ ጣሳ ውስጥ ብቻ ውሃ ይጨመራል
- ትንሽ ውሃ በአንዱ ውስጥ ብቻ በመጨመር የሚቀመጥበትን ቦታ መምረጥ
- ቦታው የሚያድገውን ጥራጥሬ ለማየት የሚመችበት ቦታ መሆን አለበት
- ጉዘዝ ሕፃን በመምረጥ በሚያስፈልግበት ጊዜ አነስተኛ ውሃ እንዲጨምርበትና ከጥቂት ጊዜ በኋላ ልዩነቱ ይታያል
- ሕፃናቱን ሰብስቡና ሀሳባቸውን እንዲገልፁ አበራታቷቸው

መልመጃ አንድ ፡-

- ሁለት ማሰሮዎችን ወስዳችሁ ጥራ ጥሬ ውስጥ ጨምራችሁ ውሃ ሁለቱንም አጠጡአቸው
- አንዱ ሳጥን ውስጥ አስቀምጡ ሁለተኛውን ግን መስኮት ላይ ብርሃን የሚያገኝበት ቦታ አድርጉ
- ሳጥኑ ትንሽ ቀዳዳ ብርሃን ማስገቢያ ይኑረው
- እፅዋቱ የፀሃይ ብርሃን እንደሚፈልጉ ያውቃል
- እፅዋቱ ብርሃን ስለሚፈልጉ ወደ ቀዳዳው በመንጋደድ እንደሚያድጉ ሕፃናቱ ይመልከቱ
- ሳጥኑን አንቀሳቅሱት እፀዋቱም አቅጣጫቸውን በመለወጥ ወደ ብርሃን ያዘነብላሉ፡፡

ምሳሌ ሁለት ፡-

- እፅዋት ሙቀት ይፈልጋሉን አዎ፣ ሁለቱን ውሃ አጠጧቸው
- አንዱን አትክልት ቅዝቃዜ ያለበት ቦታ ከመስኮቱ ውጪ ሁለተኛውን ሙቀት ያለበት መስኮት ላይ አስቀምጡት
- ቀዝቃዛ አካባቢ ያለው ሲሞት መስኮት ላይ ያለው ግን አለመሞቱን ሕፃናቱ ይመልከቱ


ምሳሌ ሶስት ፡-

- ሥሩ እንዴት እንደሚያድግ ለማየት ሙከራ መስራት
- ሁለት አበባ መትከያ አዘጋጁ
- በአንድ ውሃ የሚመጥ ቁርጥራጭ ወረቀት በሌላኛው ደግሞ የእንጨት ፍቅፋቂ አድርጉባቸው
- የእንጨት ፍቅፋቂውን ውሃ አጠጡት
- ባቄላም በቁርጥራጭ ወረቀቶቹ መሃል ትከሉ
- የተለያየ ቦታ አስቀምጡና ሥራቸውም ሆነ ግንዳቸው እንዴት እንዳደገ ይመልከቱ
- ካሮት ቁረጡ
- ውሃው ላይ አስቀምጡት
- ሥሩ ወደ ታች ማደጉን ሕፃናቱ እንዲመለከቱ ጋብዙአቸው

**143 የአለም ሙዚቃ ቅድመ ንባብ**

መርጃ መሳሪያ፡-

- የካርዶች ስብስብ፣ ጥቂት መሰረታዊ የሙዚቃ መሳሪያና አንዳንድ የሙዚቃ መጫወቻ



አላማ፡-

- ሙዚቃዊ ቃላትን እንዲያውቁ ለመርዳት
- ሙዚቃዊ አካባቢዎችን በመከፋፈል እንዲያውቁ ለማበረታታት

አቀራረብ፡-

- የተወሰኑ ሕፃናት የሙዚቃ መሳሪያዎችን ምንጣፍ ላይ እንዲያስቀምጡ መንገር
- ስለ እያንዳንዱ የሙዚቃ መሣሪያ ከሕፃናቱ ጋር መነጋገር

ለምሳሌ ከበሮ የተሠራው ከእንስሳት ቆዳና ከእንጨት መሆኑን መንገር

- ከበሮውን ስትመቱ የሚያነቃቃ ድምፅ ይሰጣችኋል በማለት ግለፁላቸው
- እንዲመለከቱ ፍቀዱላቸው
- ከሕፃናቱ ጋር አጭር ሙዚቃ ተጫወቱ
- ስለ መሣሪያው በሰስት ክፍለ ጊዜ አስተምሩአቸው

**መልመጃ አንድ**

- ሕፃኑ ከላይ እንደቀረበው የራሱን ሥራ ይሠራል

**ቋንቋ፡-**

- የሙዚቃ መሣሪያዎች ስም


**እድሜ፡-**

- 4½ ዓመት ጀምሮ

**144 የተከፋፈለ ንባብ**

**መርጃ መሳሪያ፡-**

- ሁለት ስብስብ ካርዶች የሙዚቃ መሣሪያዎችን የሚያሳዩ
- አንድ ስብስብ ስማቸው ከስር የተፃፈበት
- የሙዚቃ መሣሪያዎችን ስም የያዘ ቁርጥራጭ ካርዶች
- አንዱ ስብስብ ምንም ስም ያልያዘ



**አላማ፡-**

- ሕፃኑን በሙዚቃዊ ቃላት ለማዳበር

**አቀራረብ፡-**

- የሙዚቃ መሣሪያዎችን ስም የያዘውን ካርድ የቋንቋ ካርድ ከያዘው ማቀፊያ ጋር በተመሳሳይ መልክ ይከፋፈላል

**መልመጃ አንድ**

- የሕፃኑ ሥራ ከላይ እንዳየው ይሁን

**ስሕተትን መቆጣጠር**

- ሁለተኛ ካርድ ከነስማቸው

**እድሜ፡-**

- 4½ አመት

**ስለ ስዕል ማስታወሻ**

**የመጀመሪያ ተግባራት**

- ሕፃናቱ ለስዕል የሚመች ወረቀት ምን አይነት እንደሆነ ማሳየት
- እንዴት እንደሚጠቀሙበትና
- ከሳሉ በኋላ የት እንደሚያስቀምጡ፤ እንዴት እንደሚይዙ ወዘተ. . .ማሳወቅ

**መርጃ መሳሪያ ፡-**

- የመሳያ እርሳስና /HB ወይም B/፤ ልሙጥ ወረቀት

**አቀራረብ፡-**

- ሕፃኑ ቀላል እቃዎችን እንዴት እንደሚመለከቱ ማሳየት

**ለምሳሌ፡-**

1/ የተሠራ የአውሮፕላን ቅርፅና የመሳሰሉትን ቅርፅ መነሻ መስመር መሳል

2/ ቅጠሎች፣ ውበት ያላቸው ቅርፆችና መስመሮች

3/ ግማሽ ሽንኩርት ወዘተ . . .፡

## ቅርፅ

***መርጃ መሳሪያ***

- ከላይ የተመለከተው አይነት

**አቀራረብ ፡-**

- በእርሳሱ መቀባት፡- ለሕፃኑ በቅርበት፣ አጭርና ዚግዛግ በመሳል እንዴት እንደሚቀባ አሳዩት
- ለመነሻ የተሳለውንም እንዴት እንደሚሳል አሳዩት
- ብርሃንና ጨለማን ለማሳየት የሚያመች ስዕል በመሳል ማመልከት
- ሕፃኑ የሳለውን ስዕል በመመልከት ሲቀባ ጥላ እንዴት እንደሚሳል ማሳየት
- ለሕፃኑ እንዴት ጥላ መጨመር እንደሚቻል አሳዩት

**ስለ አቀባብ ማስታወሻ**

***መርጃ መሳሪያ፡-***

- ሸርጥ፣ የመሬት ምንጣፍ፣ የቆም ማስደገፊያ እንጨት፣ መሣያ ክፍል፣ የተወጠረ ወረቀት፣ ወረቀቱን ከማስደገፊያው ጋር ማጣበቂያ፣ ለሶስት የተለያዩ ቀለሞች መያዣ ጣሳ፣ ዱቄት ቀለም ወይም ለመቀቢያ የተዘጋጀ ቀለም፣ ሶስት ጠንካራ ብሩሾች፣ መሬትን ለማፅዳት የሚያገለግለሉ ቁሶች ናቸው

***የመጀመሪያ እንቅስቃሴ***

- ሸርጥ እንዴት እንደሚለበስና እንዴት እንደሚያወልቅ አሳዩት
- ወረቀቶችን የት እንደሚያገኝ፣ እንዴት ከማስደገፊያው ጋር ወረቀቱን እንደሚያጣብቅ ማሳየት፣ ብሩሽ አያያዝ ማሳየት፣ የቀለሙን ጣሳ የሚያስቀምጥበትን ስፍራ ማሳየት
- ስእሉ ላይ ያሉትን ጠብታዎች ማፅዳት፣ ሕፃኑ ጨረስኩ ካለ በኋላ የት እንደሚያስቀምጥ እንዲሁም እጅ ማፅዳት እንዳለበት ማስረዳት

**አቀራረብ ፡-**

- ቀላል ምስሎችን መቀባት ለምሳሌ በትክክል የተዘጋጁ የጂኦሜትሪ ምስሎች
- አቀራረቡ ላይ ስለ አሳሳል ከቀረበው ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ልዩነቱ መጠኑ ብቻ ነው
- የሚስቡ ቅርፆችን በመጨረሻ እንቀባለን

**አቀራረብ፡-** ጠንከር ያሉ ቀለሞችን መቀባት

- ቀለል ያለ ክብ መቀባት፣ ወደ አግድም መሙላት ወይም ወደ ታች በቀለም የተሰመረ
- በመቀጠል በትንሹ መቀባት፣ ከፍ ያለ ምስል መቀባት እያለ ማሳደግ

**አቀራረብ፡-**

- ቀለም መደባለቅ
- ሁለት ዋንኛ ቀለሞችን በመደባለቅ ሌላ ሶስተኛ ቀለም ማግኘት

## የመስሎ መጫወት ጨዋታ እቅድ

| | |
|---|---|
| የጨዋታው አይነት | የመስሎ መጫወት ጨዋታ |
| የጨዋታው ርዕስ | ሕፃናቱ በመረጡት |
| የጨዋታው መሣሪያ | በሕፃናቱ ምርጫ |
| የጨዋታው ሂደት | ዝርዝሩ |
| የጨዋታው ሕግ | በመስሎ መጫወት ጨዋታና በግንባታ ጊዜ ሕግ የለውም |

## ቲያትራዊ /ድራማዊ ጨዋታ/

የመምህሩን ሙሉ አመራር ስለሚጠይቅ በይዘቱ ከግንባታና ከመስሎ መጫወት ጨዋታ ይለያል መምህሩ ያዘጋጀውን ዕሁፍ /በዕሁፍ/ ውስጥ ያሉትን ገፀ ባህሪ በጥንቃቂ መስራት ስላለባቸው የመምህሩ ጥንቃቂ ያስፈልጋል::

| የእንቅስቃሴ ጨዋታዎች | ትምህርታዊ ጨዋታዎች |
|---|---|
| አረንጓዴ | ካርታ |
| ማሀረቤን | የጠፋውን ፈልግ |
| ትልቁ | እንቆቅልሽ |
| እዬ ሰሌ | እንኪያ ሰላንተያ |
| ልጅ ለመፈለግ መጥተናል | |
| እረ አምሳለ | |
| ትራትራ ፓስቲላ | |
| ንጉስ ንጉስ ሆይ | |
| ያሰቆብ | |

| ግንባታ ጨዋታ | ድራማዊ ጨዋታ |
|---|---|
| በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ ይደራጃል በሕፃናቱ ፍላጎት መገንባት፤ ማፍረስና መደርደር መለማመድ | መምህሩ በሚያዘጋጀው (ስነ-ዕሁፍ) ውስጥ ያሉትን ገፀ ባህሪያት |